# ትምህርት 12

1. ሰይጣን ሔዋንን ሊያስት ሲመጣ ራሱን የደበቀው እንዴት ነበር?

ሀ- በእባብ ውስጥ በመሆን።

2. ሔዋን ሲያነጋግራት የነበረው ሰይጣን መሆኑን ታውቅ ነበር?

ሀ- አታውቅም።

3. ሰይጣን በእባብ ውስጥ የተደበቀው ለምንድን ነው?

ሀ- ሔዋንን ሊያጠምድ ስለ ፈለገ ነው።

ለ- ሔዋንን ሊያስት ስለ ፈለገ ነው።

ሐ- ሔዋንን ሊያጠፋት ስለ ፈለገ ነው።

4. ዛሬም ሰይጣን ሰዎችን ለማጥመድና ለማሳት እየሞከረ ነው?

ሀ- አዎን።

5. ሰይጣን ሰዎችን ለማጥመድና ለማሳት የሚሞክረው እንዴት ነው?

ሀ- ሰይጣን የሚጠቀምበት አንደኛው መንገድ በልባችን ውስጥ ለእኛ በመናገር ነው።

ለ- ሰይጣን የሚጠቀምበት ሁለተኛው መንገድ በሌሎች ሰዎች በኩል ለእኛ በመናገር ነው።

ሐ- ሰይጣን የሚጠቀምበት ሦስተኛው መንገድ በአጋንንቱ በኩል ለእኛ በመናገር ነው።

6. እግዚአብሔር ለአዳም መልካምና ክፉ ከሚያሳውቀው ዛፍ ፍሬ ከበሉ ምን እንደሚሆኑ ነገረው?

ሀ- እንደሚሞቱ።

7. ሰይጣን ለሔዋን መልካምንና ክፉን ከሚያሳውቀው ዛፍ ፍሬ ከበሉ ምን እንደሚሆኑ ነገራት?

ሀ- እንደማይሞቱ።

ለ- እንደ እግዚአብሔር እንደሚሆኑ።

8. ሰይጣን እግዚአብሔር ምን ብሎ ጠራው?

ሀ- ውሸታም።

9. አዳምና ሔዋን ኃጢአት ከሠሩ በኋላ ዕራቁት መሆናቸውን ሲገነዘቡ ምን አደረጉ?

ሀ- የቅጠል ልብስ ሠሩ።

10. አዳምና ሔዋን ኃጢአት ከሠሩ በኋላ እግዚአብሔር ሊጎበኛቸው ወደ እነርሱ ሲመጣ ምን አደረጉ?

ሀ- ከእግዚአብሔር ተደበቁ።

11. ከእግዚአብሔር መደበቅ ይቻላል?

ሀ- አይቻልም። እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ስለሚገኝ።

12. ሰይጣን የሚጠላው ማንን ነው?

ሀ- ሰይጣን የሚጠላው እግዚአብሔርንና ሰዎችን ሁሉ ነው።

13. ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል እንድትሰሙ ይፈልጋል?

ሀ- አይፈልግም።

14. ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል እንዳትሰሙ የሚፈልገው ለምንድን ነው?

ሀ- ሰይጣን ሰዎችን ሁሉ ስለሚጠላና ወደ ዘላለሙ የእሳት ባሕር እንዲጣሉ ስለሚፈልግ ነው።

- አዳምና ሔዋን ትዕዛዙን እምቢ ካሉ በኋላ እግዚአብሔር ምን አደረገ?

ዘፍጥረት 3፡9

9 - እግዚአብሔር አምላክ ግን አዳምን ተጣርቶ፣ «የት ነህ?» አለው።

- አዳምና ሔዋን ትዕዛዙን እምቢ ካሉ በኋላ እግዚአብሔር አዳምን ጠራው።

- እግዚአብሔር አዳምን የጠራው አዳም የት እንዳለ ስላላወቀ ነበር?
- አይደለም።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ያውቃል።
- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ያያል።

- ከእግዚአብሔር መደበቅ የሚችል ማንም የለም።

- እግዚአብሔር አዳምን የጠራው ለምን ነበር?

- እግዚአብሔር አዳምን የጠራው ወደ እርሱ መጥቶ ኃጢአቱን እንዲናዘዝ ነበር።

- እግዚአብሔር አዳምን የጠራው ወደ እርሱ መጥቶ የእርሱን ትዕዛዝ እምቢ ማለቱን እንዲያምን ነበር።

- እግዚአብሔር አዳምን የጠራው ወደ እርሱ መጥቶ ሰይጣንን መታዘዙን እንዲያምን ነበር።

- እግዚአብሔር አዳምን ሊጠራው የቻለው እንዴት ነው?

- እግዚአብሔር አዳምን ስለ ፈጠረ ነው።
- አዳም የእግዚአብሔር ስለ ሆነ ነው።

- እግዚአብሔር አዳምን የፈጠረው እንዲታዘዘው ስለ ሆነ ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ሊጠራ የቻለው እንዴት ነው?
- እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ስለ ፈጠረ ነው።

- ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ስለ ሆኑ ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ የፈጠረው እንዲታዘዙት ስለ ሆነ ነው።

- እግዚአብሔር አልተለወጠም።
- እግዚአብሔር ዛሬም ሰዎችን ይጠራል።

- እግዚአብሔር ዛሬ ሰዎችን የሚጠራው እንዴት ነው?

- አንደኛ እግዚአብሔር ሰዎችን በፍጥረቱ አማካይነት ይጠራል።

- የእግዚአብሔር ፍጥረት እግዚአብሔር መኖሩን ሁሉንም ነገር መፍጠሩንና እኛም ለእርሱ እንድንታዘዝ እንደሚፈልግ ያሳየናል።

- ሁለተኛ እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ በርሱ መጽሐፍ፥ ማለትም በመጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት ይጠራል።

- የእግዚአብሔር መጽሐፍ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ለእናንተ የእግዚአብሔር መልእክት ነው።

- የእግዚአብሔር መጽሐፍ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ለእናንተ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

- እግዚአብሔር አዳምን በጠራው ጊዜ አዳም ምን አለ?

ዘፍጥረት 3፡10

10- አዳምም «ድምፅህን በአትክልቱ ስፍራ ሰማሁ፤ ራቁቴን ስለ ሆንሁ ፈራሁ፤ ተሸሸግሁም» ብሎ መለሰ።

- አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን የፈሩት ለምን ነበር?

- የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እምቢ ስላሉ።

- አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡

- ሌባ የሰውን በቆሎ እየሰረቀ የእርሻው ባለቤት ቢመጣበት፥ ሌባው አይሸሸግም?

- ይሸሸጋል።

- አዳምና ሔዋን ኃጢአት ስለ ሠሩና ለእግዚአብሔር ስላልታዘዙ ከእግዚአብሔር ተሸሸጉ።

- ታዲያ እግዚአብሔር አዳምን ምን አለው?

ዘፍጥረት 3፡11

11- እግዚአብሔርም “ዕራቁትህን መሆንህን ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ ብዬ ካዘዝሁህ ዛፍ በላህን?” አለው።

- እግዚአብሔር አዳም ከዛፉ ፍሬ መብላት አለመብላቱን ለምን ጠየቀው?

- አዳም ከፍሬው መብላቱን እግዚአብሔር አያውቅም ነበር?

- ያውቃል።

- ታዲያ እግዚአብሔር አዳም ከዛፉ ፍሬ መብላት አለመብላቱን ለምን ጠየቀው?

- እግዚአብሔር የጠየቀው አዳም ወደ እርሱ መጥቶ ኃጢአቱን እንዲናዘዝ ፈልጎ ነው።

- እግዚአብሔር የጠየቀው አዳም ወደ እርሱ መጥቶ እርሱን አለመታዘዙን እንዲያምን ፈለጎ ነው።

- እግዚአብሔር የጠየቀው፥ አዳም ወደ እርሱ መጥቶ ሰይጣንን መታዘዙን እንዲያምን ፈለጎ ነው።

- እግዚአብሔር አዳምን መጠየቅ የቻለው እንዴት ነው?
- አዳምን የፈጠረው እርሱ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

- ሰዎችን ሁሉ የፈጠረው እግዚአብሔር ስለሆነ፥ ሁሉንም ሰውን መጠየቅ ይችላል።

- አንድ ቀን እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ይጠይቃል ሁሉም ሰው ለእግዚአብሔር መልስ ይሰጣል።

- እግዚአብሔር አዳምን ሲጠይቀው አዳም ምን መልስ ሰጠው?

ዘፍጥረት 3፥12-13

12- አዳምም፣ «ይህች ከእኔ ጋር እንድትኖር የሰጠኸኝ ሴት፣ እርሷ ከዛፉ ፍሬ ሰጠችኝና በላሁ» አለ።
13- እግዚአብሔር አምላክ ሴቲቱን፣ «ይህ ያደረግሽው ምንድን ነው?» አላት። እርሷም፣ «እባብ አሳሳተኝና በላሁ» አለች።

- አዳም ሔዋንን ከሰሰ፤ ሔዋንም እባቡን ከሰሰች።
- እግዚአብሔር እውነቱን ያውቃል።

- ከእግዚአብሔር የተሰወረ እውነት የለም።

- አንድ ሰው ሰርቆ ቢያዝ ምን ያደርጋል?
- ሌላውን ሰው ጥፋተኛ ለማድረግ ይሞክራል።

- ምናልባት እኛም ጥፋታችንን በሌሎችን ላይ በማዞር፥ ሰዎችን ልናታልል እንችላለን።

- ጥፋታችንን በሌሎች ላይ በማዞር እግዚአብሔርን ግን ልናታልለው አንችልም።

- እግዚአብሔር ሁል ጊዜም እውነቱን ያውቃል።

- እግዚአብሔር ሁልጊዜም የማይታዘዙትን ይቀጣል።
- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ኃጢአት የሚሠሩትን ይቀጣል።

- በመጀመሪያ እግዚአብሔር እባቡን ቀጣው።

ዘፍጥረት 3፥14

14- እግዚአብሔር አምላክ እባብን እንዲህ አለው፤ «ይህን ስለ ሠራህ፣ «ከከብቶችና ከዱር እንስሳት ሁሉ ተለይተህ የተረገምህ ሁን፤ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ፣ በደረትህ እየተሳብህ ትሄዳለህ። ዐፈርም ትበላለህ።»

- እግዚአብሔር እባቡን የቀጣው እንዴት ነበር?

- እባብ በደረቱ እየተሳበ እንዲሄድ በማድረግ።

- እግዚአብሔር እባቡን ለምን ቀጣው?

- እባቡ ሔዋንን አላናገራትም።

- ሔዋንን ያናገራት ሰይጣን ነው።

- ታዲያ እግዚአብሔር እባቡን ለምን ቀጣው?

- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ ስለሚቀጣ፣

- ሰይጣን እባቡን ኃጢአትን ለመሥራት ስለ ተጠቀመበት።

- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ ይቀጣል።

- ቀጥሎ፥ እግዚአብሔር ሔዋንን ቀጣት።

ዘፍጥረት 3፡16

16- ሴቲቱንም እንዲህ አላት፤ «በምጥ ጊዜ ጭንቅሽን አበዛለሁ፤ በሥቃይም ትወልጃለሽ፤ ፍላጐትሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፤ እርሱም የበላይሽ ይሆናል።»

- እግዚአብሔር ሔዋንን የቀጣት እንዴት ነበር?

- ሔዋን በጭንቅ እንድትወልድ በማድረግ።

- የሔዋን ቅጣት የሁሉም ሴቶች ቅጣት ነው።

- ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሁሉም ሴቶች የሚወልዱት በጭንቅ ነው።

- አሁንም ቀጥሎ፥ እግዚአብሔር አዳምን ቀጣው።

ዘፍጥረት 3፡17-19

17- እግዚአብሔር አምላክ አዳምንም እንዲህ አለው፤ «የሚስትህን ቃል ሰምተህ፣ <ከእርሱ አትብላ> ብዬ ያዘዝሁህን ዛፍ በልተሃልና፣ ከአንተ የተነሣ ምድር የተረገመች ትሁን፤ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ምግብህን ጥረህ ግረህ ከእርሷ ታገኛለህ።

18- ምድርም እሾኽና አሜኬላ ታበቅልብሃለች፤ ከቡቃያዋም ትበላለህ።

19- ከምድር ስለ ተገኘህ፣ ወደ መጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ እንጀራህን በፊትህ ላብ ትበላለህ፤ ዐፈር ነህና ወደ ዐፈር ትመለሳለህ። »

- እግዚአብሔር አዳምን የቀጣው እንዴት ነበር?

- አዳም መሬትን ብዙ ላብ በማፍሰስ ያርሳል ሆኖም ጥቂት ምርት ብቻ ያገኛል።

- የአዳም ቅጣት የሁሉም ወንዶች ቅጣት ነው።

- አሁን ሁሉም ሰው መሬትን ለማረስ ብዙ ላብ ያፈስሳል፤ የሚያገኘው ምርት ግን ጥቂት ነው።

- እግዚአብሔር አዳምን በሌላ በምን ቀጣው?
- እግዚአብሔር መላውን ምድር ረገመ።

- እግዚአብሔር ምድርን የመርገሙ ምልክቶች ምንድን ናቸው?

- ብዙ እሾኾችና ዐረሞች መኖራቸው፤
- ብዙ ድርቅና የጐርፍ አደጋዎች መኖራቸው፤
- ብዙ መርዛማ ተክሎችና እባቦች መኖራቸው፤

- እንስሳት ሰዎችን መንከሳቸው፤
- በሰዎች ላይ አድካም ሥራ መኖሩ፤

- ሰዎች መታመማቸው፤
- ሰዎች መሞታቸው።

- አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ስላልታዘዙ ምድር ተረገመች።

- አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ስላልታዘዙ ምድር በክፉት ተሞላች።

- አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ስላልታዘዙ ሁሉም ሰው ይሞታል።
- ላለመታዘዝ የእግዚአብሔር ቅጣት የዘላለም ሞት ነው።

- ለኃጢአት እግዚአብሔር የሰጠው ቅጣት የዘላለም ሞት ነው።

- አዳምና ሔዋንን ከቀጣቸው በኋላ እግዚአብሔር የተናገረውን እስቲ እናንብብ።

ዘፍጥረት 3፡15

15- እግዚአብሔር አምላክም እንዲህ አለ በአንተና በሴቲቱ፣ በዘርህና በዘሯ መካከል፣ ጠላትነትን አደርጋለሁ። እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ተረከዙን ትቀጠቅጣለህ። »

- እግዚአብሔር የሚናገረው ለማን ነበር?
- እግዚአብሔር የሚናገረው ለሰይጣን ነበር።

- እግዚአብሔር ለሰይጣን ምን አለው?

- እግዚአብሔር ያለው፥ ሰይጣን ተረከዙን ቢቀጠቅጥ እንኳን፥ የሰይጣንን ራስ የሚቀጠቅጥ እንደሚመጣ ነው።

- የሰይጣንን ራስ የሚቀጠቅጠው ማነው?

- አዳኙ ነው።

- እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከቀጣ በኋላ ምን ሊያደርግ ቃል ገባ?

- እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከቀጣ በኋላ አዳኙን እንደሚልክ ቃል ገባ።

- አዳኙ የሚመጣው ምን ለማድረግ ነው?

- አዳኙ የሚመጣው ሕዝቡን ከኃጢአት ኃይል ለማዳን ነው።
- አዳኙ የሚመጣው ሕዝቡን ከሞት ኃይል ለማዳን ነው።
- አዳኙ የሚመጣው ሕዝቡን ከሰይጣን ኃይል ለማዳን ነው።

- አዳኙ የሚመጣው ሰይጣንን ለመዋጋት ነው።

- ሰይጣን አዳኙን ያቆስለዋል ነገር ግን አዳኙ ሰይጣንን ያሸንፈዋል።

- አዳኙ የሚሆነው ማን ነው?
- አዳኙ የሚሆነው ከድንግል የሚወለደው ልጅ ነው።

- እግዚአብሔር አዳኙን ለመላክ ቃል የገባው ለምንድን ነው?
- እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው እጅግ ስለሚወድድ ነው።

- አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔር ምህረትይገባቸው ነበር?
- አይገባቸውም ነበር።

- ለአዳምና ሔዋን የእግዚአብሔር ምህረት የማይገባቸው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔርን ስላልታዘዙና የሰይጣንን ምክር ስለሰሙ ነው።

- ለአዳምና ሔዋን ያለመታዘዝ የሚገባው ቅጣት ምን ነበር?
- ላለመታዘዛቸው የሚገባው ቅጣት የዘላለምን ሞት ነበር።

- ለአዳምና ሔዋን ያለመታዘዝ የሚገባው ቅጣት ሞት ነበር።

- ነገር ግን እግዚአብሔር እነርሱን ለማዳን አዳኝ እንደሚልክ ቃል ገባ።

- አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡
- አንድ ወደ ሞት የቀረበ ሰው ወደ ቤታችሁ መጣ፥ እንበል።

- እናንተ ምግብ ሰጣችሁለት፤ መድኃኒትም ገዛችሁለት።
- ይህ ሰው ከእናንተ ጋር ብዙ ቀን ቆየ።

- በመጨረሻም ይህ ሰው ከበሽታው ዳነ።

- ሰውዬው ከመመለሱ በፊት ላማችሁን ሰርቆ ይሄዳል።

- በኋላም ሰውዬው እንደ ገና ታሞ፥ ሊሞት ተቃርቦ ወደ እናንተ ተመልሶ ይመጣል።

- እናንተም አሁንም ምግብ ሰጣችሁለት፤ መድኃኒትም ገዛችሁለት።
- ሰውዬው እንደገና ከበሽታው ይድናል።

- ይህ ሰው ላማችሁን ስለ ሰረቀ ቅጣት ይገባው ነበር።

- ይሁን እንጂ ሰውዬው ከበሽታው እንዲድን እንደገና ረዳችሁት።

- ለአዳምና ሔዋን ያለመታዘዝ የሚገባው ቅጣት ሞት ነበር።